# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 208 ግንቦት 2 2004 ገጽ 1

ግንቦት 7፣ በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ የሚመጣበት ወቅት ላይ ደርሰናል ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ወቅት ለሚመጡ የመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያዎችና ማዘናጊያዎች ጆሮዎቹን መድፈን አለበት ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ - ሙስሉሙም ክርስቲያኑም - በመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያዎችና መሸንገያዎች ሳይበገር ለእኩልነትና ለፍትህ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብሎ ያምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት በኢትዮጵያ የወያኔው አገዛዝ በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ ለማስቆም ሁላችንም በጋራ እንነሳ ሲል ጥሪ አቀረበ

ጥምረት ለነጻነት፡ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ፤ ያለፉት ሶስት ወራት የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲገመገም የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በህዝባችንንና በአገራችን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና መከራ ሌላ እምርታ እያሳየ መሆኑን ገልጾ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተነሱ የሙብት ጥያቄዎች ከቁጥጥር ውጭ የሆነበት የወያኔው አገዛዝ “የሰሜን አፍሪካ አይነት ህዝባዊ አብዮት ተቀስቅሶ ሊውጠኝ ነው” በሚል ፍራቻ በዜጎች ላይ ወደር የለሌው አፈና እርምጃ ከመውሰድ አልፎ ጭካኔ የተሞላበት ግዲያና እስራቱን አጠናክሮ ቀጥሎበታል ሲል ወንጅሎአል።

ወያኔ በልማት ስም አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ከመኖሪያ ቄያቸው በግፍ ማፈናቀሉ ሳያንሰው ዋልድባን የመሰሳሉ የሃይማኖት ቦታዎችን በመድፈር በአለም ደረጃ እውቅናና አድናቆት የተስጣቸውን የሀገርቱን የሃይማኖትና የታሪክ ቅርሶች በማውደም ለኢትዮጵያና ለእምነቱ ተከታዮች ያለውን ንቀትንና ጥላቻ በገሃድ እያሳየ ነው የሚለው የጥምረቱ መግለጫ መለስ ዜናዊ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ያነሱትን የሙብት ጥያቄ ክብደት ስጥቶ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ጥያቄውን በማንቋሸሽና በማናናቅ በአለም ከሚታየው አክራሪነት ጋር በመፈረጅ የምእራቡን አለም ቀልብ ለመሳብና ለዲፕሎማሲያዊ ፍጆታ ለመጠቀም ላይ ታች እያለ መሆኑን አጋልጦአል።

በመቀጠልም ሁለቱ አንጋፋ ሃይማኖት ተከታዮችን እርስ በርስ በጠላትነት እንዲተያዩ ወያኔ ሆን ብሎ እየሸረበ ካለው ተንኮል ባሻገር የሙስሊሙን ህብረተሰብ እርስ በርሱ ለማፋጀት እየተካሄደ ያለው ተንኮል የመለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ እኩይነት ማረጋገጫ ነው ያለው የጥምረት መግለጫ ፤ ባለፈው ሳምንት በአርሲ ውስጥ አሳሳ ከተማ መስጂድ በተሰበሰበው ህዝብ ላይ በተከፈተው ተኩስ የተጨፈጨፉ ንጹሃን ዜጎች የወያኔን ምንነት ማረጋገጫ ነው ብሎአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ጥምረት ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 3 ያንቡ

## ወያኔ ተጨማሪ ፖሊስና መካለከያ ሰራዊት ውጥረት ወደነገሰበት ጋምቤላ ለማዝመት እንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ተዘገበ

የግንቦት7 ምንጮች እንደገለጹት ወያኔ በጋምቤላ እየተስፋፋ የመጣውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለመምታት እንዲያስችለው ተጨማሪ ሠራዊት ለማዝመት የክልሉ ፕሬዝዳንት አድርጎ ባስቀመጠው አሞድ አባንግ አማካይነት በአድራሻ ለመለስ ዜናዊ፣ ለኢህአዴግ ጽህፈት ቤት፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለፌደራል ፖሊስና ለመከላከያ ሰራዊት ማመልከቻ እንዲገባ አስደርጎአል።

የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ በፈለገበት ቦታና ጊዜ ሰራዊቱን የማንቀሳቀስ ብቸኛ ሙብት እያለው በክልሉ ፕሬዝዳንት በኩል ጥያቄው እንዲቀርብ ማስደረጉ በሲቪሎች ላይ ለሚፈጸመው ጭፍጨፋ ልክ በ1996 በአኝዋክ ንጹሃን ዜጎች ላይ ለተፈጸመው ዘር ማጥፋት ሃላፊነቱን በክልሉ ባለሥልጣናት ላይ ለማላከክ እንደተሞከረው ለማድረግ ይረዳል በሚል ስሌት እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

የክልሉ ፕሬዚዳንት አሞት አባንግ በመለስ ዜናዊ ግፊት ለፈደራሉ እንዲጽፍ በተደረገው በዚህ ደብዳቤ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ዝቅጠት እና የአመራር ብልሹነት ያለ በመሆኑ የፌደራል መንግስት የአመራር ለውጥ በማድረግ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰቢያ ሰጥቶአል ተብሎአል።

ወያኔ ተጨማሪ የወታደር ሃይል ለማዝመት ዝግጅት እያደረገ ባለበት በዚህን ሰዓት እስካሁን በክልሉ ተመድቦ ያለው የፖሊሲና የመከላኪያ ሰራዊት በጋምቤላ ንጹሃን ዜጎች ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ አሰቃቂ ግዲያ፤ እስራትና ድብደባ እየፈጸመበ እንደሚገኝ የአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ አስታወቀ።

ባለፈው ሳምንት ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ ም በጋምቤላ - አቦቦ ወረዳ ፖኪዶ ቀበሌ በጠራራ ፀሃይ ንፁሃን በጥይት ተደብድበው መገደላቸውን ተከትሎ የአካባቢው ህዝብ ብሶትና ቁጣ ከመቼውም በላይ ገንፍሎ እየወጣ ነው ያለው የጋራ ንቅናቄው መረጃ የአካባቢው ህዝብ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በሃይማኖት ሽፋን በግልጽና በህቡእ የሃገሪቱን ሰላም ለማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ አካላት ባለቸው የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ርምጃ እንደሚወስድ የወያኔ መንግስት ዛተ

ዛቻውን በተላላኪው የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማሪያም በኩል የሰነዘረው ወያኔ ጥቂት አክራሪዎች ብዙሀኑን የእስልምና እምነት ተከታይ በማስፈራራትና በመደለል የአክራሪነት እንቅስቃሴ እያካሄዱ ነው ፤ ይህን እንቅስቃሴያቸው ደግሞ አዲስ አበባን በማእከልነት በመጠቀም በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች በተለይም በኦሮሚያ ባሉ ሙስሊሞች ላይ በሃይል ለመጫን እየሰሩ ነው ሲል በበርካታ ሚሊዮኖች ለሚቆጠሩት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያለውን ንቀት የሚያሳይ መግለጫ መስጠቱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ዘግቧል።

ዘጋቢያችን እንዳለው ወያኔ በጥያቄ አለን ሽፋን የተሸሸጉና ከጀርባ ድብቅ የትርምስ አጀንዳ ያነገቡ ግለሰቦች የተሰጣቸውን ተገቢ ምላሽ ወደጎን በመተው ህዝበ ሙስሊሙን እያደናገሩት በማለት የሙስሊሙን ማህበረሰብ ተወካዮች ነጥሎ ለመምታት አነጣጥሯል። ይህንንም ነጥሎ የመምታት እቅድ በሙስሊሙ ጥቆማ የተፈጸመ ነው ለማለትና ለመከፋፈል ህዝበ ሙስሊሙ እነዚህን አክራሪዎች በመምከርና በማጋለጥ የተለመደ ትብብሩ እንዲያደርግ ጥሪ እናስተላልፋለን በማለት ጊዜ ያለፈበትን ዘዴውን ለመጠቀም ሞክሯል።

ሽፈራው ተክለማሪያም ለፓርላማ ተብዬ ሚያዚያ 30/ 2004 ዓ.ም በሰጠው በዚሁ ማብራሪያ እነዚህ ጥቂት አክራሪዎች ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከመንግስት ጋር ለማጋጨት በርካታ የማደናገሪያ አጀንዳዎችን በጋዜጦች፣በመጽሄቶችና በኤሌክትሮስ ሚዲያዎች እያስተጋቡ ነው በማለት ሰላማዊውን የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥያቄ ፖለቲካዊ ገጽታም ሊያላብሰው ጥሯል።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ ጥያቄ እጅግ በጣም ግልጽና የማያሻሙ ናቸው፤ባልመረጥነው መጅሊስ አንተዳደርም፣የአህባሽ አስተምህሮት ያለፍላጎታችን አይጫንብን የሚሉ ። ይህ እንዴት አክራሪነት ሊሆን እንደሚችልና ፖለቲካዊ ገጽታ ሊላበስ እንደሚችል አይገባኝም፤ በግለ ሰብ ደረጃ የአክራሪነት ስሜት ያላቸው ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ ነገርግን የነዚህ ግለሰቦች አመለካከት ከአሁኑ የመላ ህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም ሲሉ አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተወካዮች ሰሞኑን ባወጡት መግለጫ ሽፈራው ተክለማሪያምን ጨምሮ አንድአንድ ባለስልጣናት ሆን ብለው ሰላማዊውን የሙስሊም ማህበረሰብ ጥያቄ ከአክራሪነት ጋር በማያያዝና ፖለቲካዊ ቀለም በመቀባት ህጋዊ ላልሆነው መጅሊስ ድጋፋቸውን እየሰጡ መሆኑን መግለጻቸው ይታወሳል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በመለስ ዜናዊ የሚመራው አገዛዝ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል በመፈጽምና የህዝቡን ሰብአዊ መብቶች በመጣስ መንግሥታዊ ሽብር እየፈጸመ መሆኑን አንድ አለም አቀፍ ድርጅት ያካሄደው ጥናት ይፋ አደረገ

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ የዳሰሰው ይህ ጥናት ይፋ እንዳደረገው ዜጎችን ያለበቂ ምክንያት በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ማሰቃየትና ወህኒ መወርወር የኢትዮጵያው አገዛዝ የተለዩ አመለካከቶችንና ድምጾችን ለማፈን የሚጠቀምባቸው የጥቃት ስልቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ ማናቸውም በዴሞክራሲ መብቴ እጠቀማለሁ የሚል፣ሰብዓዊና የሞራል መብቶቹ እንዲከበሩ የሚጠይቅ ዜጋ ሁሉ ወንድ ሴት ሳይል የዚህ ጥቃት ሰለባ እንደሆነና ጥቃቱ የመለስን አምባገነን ስርዓት የሚቃወሙና በአማራጭ ፖለቲካ ፓርቲነት በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በስርዓቱ እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችንና ወንጀሎችን በብእራቸው ለአደባባይ የሚያበቁ በሀገር ውስጥና በውጪ የሚገኙ ጋዜጠኞችም ላይ ያነጣጠረ ነው ።

ግርሃም ፒብልስ የተባሉ ባለሙያ ህገ ወጥ እስር በኢትዮጵያ፤ማሸበር፣ማሰቃየትና በቁጥጥር ስር ማዋል በሚል ርእስ እነሆ ባሉት በዚህ ጥናት እንደገለጹት ሽብርተኝነት የኢትዮጵያ መንግስት ኢ-ፍትሃዊነቱን፣እብለቱንና ወንጀሉን ለመሸፈን የሚጠቀምበት ትልቅ መጋረጃ ነው።በኢትዮጵያ ሽብርተኛ ድርጅት አቆጥቁጧል ከተባለም በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ወንጀል በመፈጽምና የህዝቡን ሰብዓዊ መብቶች በመጣስ መንግስታዊ ሽብር እየፈጸመ ያለው በመሰስ ዜናዊ የሚመራው ኢህአዴግ ነው።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያና ማዘናጊያዎች ለፍትህ እና ለእኩልነት የተነሳን ሕዝብ ትግል ሊገቱት አይችሉም

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ከፌደራሊዝም ጋር የማይተዋወቅ ቢሆንም እንኳን “የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር” የሚባል መ/ቤት አለው። የሚኒስትርነት ደረጃ የተሰጠው ይህ መሥሪያ ቤት እስከዛሬ የመለስ የስለላ ተቋምና የፌደራል ፓሊሲ ተቀጥያ ነበር። ሰሞኑን ግን የመለስ ዜናዊ “አፈ-ንጉሥ” ሆኖ በመቅረብ ሰላማዊ ሕዝብን የማስፈራራት አዲስ የሥራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር አዲሱ ሥራውን የጀመረውም በሙስሊም ማኅበረሰብ አባላት ላይ ማስፈራሪያና ዛቻ ያዘለ መግለጫ በማውጣት ነው። በምርጫ 97 ማግሥት እንዲህ ዓይነቱን ማስፈራሪያ የሰጠው ራሱ መለስ ዜናዊ ነበር። አሁን ግን አዲሱ አፈ-ንጉሥ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተናገረለት።

እንደ አፈ-ንጉሡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መግለጫ ከሆነ፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ያልሰጠው በልማት ሥራዎች በመጠመዱ ምክንያት ነው። ይህ በከፊልም ቢሆን እውነት ነው። መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ ራሳቸውን፤ ማለትም የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትን፤ በማበልጸግ ሥራ ላይ መጠመዳቸው ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት፣ ቀንና ሌሊት ከድሃው ኢትዮጵያዊ ሲዘርፉና ሲያዘርፉ፤ ሲበሉና ሲያከማቹ፤ በድሃው ድካምና ስቃይ ሲዝናኑ እነሆ ሃያ ዓመት አልፏቸዋል። “ልፋታቸው” መና አልቀረም። ዛሬ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቷ ባሉ ከተሞች እነሱ ባለ ህንፃዎችና ኩባንያዎች ሌሎች ደግሞ ተፈናቃዮች ሆነዋል። ከከተሞችም አልፈው በገጠር እነሱ የሰፋፊ እርሻዎች ባለንብረቶች፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ተመጽዋቾች ሆነዋል። የመግለጫው ስህተት ለትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት እድገት የተደረገው ጥረት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን የተደረገ አስመስሎ የሚናገር መሆኑ ነው። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት እያደር እየፋፉ መሆናቸው እውነት ቢሆንም ኢትዮጵያዊያን ከመለስ አገዛዝ የተረፋቸው ድህነት፣ ረሃብ፣ ስደት፣ መፈናቀል፣ ተስፋ ማጣትና የኑሮ መመሰቃቀል መሆናቸው ግን መግለጫው አይጠቅስም።

ቀጥሎም መግለጫው “ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ የሃይማኖት እኩልነት ተከብሯል” በማለት ይቀልዳል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሃይማኖት ተቋማትን የአገዛዙ መሣሪያዎች እንዳደረጋቸው በይፋ እየታወቀ ለወያኔ ባዕድ ስለሆነው “እኩልነት” ይናገራል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሃይማኖቶች ብቻ ሳይሆን በሰው ልጆች እኩልነት እንኳን የማያምን እጅግ ዘረኛ የሆነ አገዛዝ እንደሆነ ይታወቃል። አገዛዙ ራሱን የአንድ ምርጥ ዘር ተወካይ አድርጎ የሾመ ሆኖ እያለ እንደምን አድርጎ ስለእኩልነት ግንዛቤ ሊኖረው ይችላል? የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሃይማኖት ተቋማትን ብቻ ሳይሆን ከተቻለው ሃይማኖቶችንም ለዘረኛ አገዛዙ መጠቀሚያነት እንደሚያውላቸው በተደጋጋሚ የታየ ሃቅ ነው። ለምሳሌ አህባሽ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ “ምርጥ” ሃይማኖት ነው። “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንዲሉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአለበት “እኩልነት” ብሎ ነገር የለም።

መግለጫው ስለእድገት እና ሃይማኖቶች እኩልነት የተንሸዋረሩ ነገሮችን ካነሳ በኋላ በቀጥታ የሚያመራው ወደ ማስፈራራት ነው። መግለጫው ሙስሊም ዜጎቻችንን በአሸባሪነት ይከሳል። በአወሊያ መስጊድ ድምፃቸውን በማሰማት ላይ ያሉት ሙስሊሞች የእስላም መንግሥት ሊያቋቁሙ የሚፈልጉ አክራሪዎች ናቸው በማለት የክርስቲያኑን ልብ ለመስረቅ ይጥራል። ቀጥሎ ደግሞ መለስ የሚቃወሙትን ሁሉ ወደሚጠራበት “የከሰሩ ፓለቲከኞች” ወደ ሚለው ተራ አባባል እና ድንፋታ ይዘቅጣል። በምዕራብ አርሲ ዞን በገደባ አሳሳ ወረዳ አሳሳ ከተማ የመለስ ገዳዮች በንጹሃን ዜጎች ለፈጸሙት የግድያ ወንጀል ተበዳዮችን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። የመለስ አገዛዝ ተበዳይ ለመበደሉ ተጠያቂ አድርጎ ማቅረብ የቆየ ልማዱ እንደሆነ ይታወቃል። በምርጫ 97 ማግሥትም ህፃን ነቢዩም ባንክ ሊዘርፍ ነበር መባሉን አንረሳም። ዛሬም በአሳሳ ከተማ በግፍ የተጨፈጠፉ ወገኖቻችን የእስላም መንግሥት ሊያቋቁሙ ነበር መባሉ ፈጽሞ ሊገርመን አይገባም።

ይህ መግለጫ በምርጫ 97 ማግሥት ከቀረበው መግለጫ የሚለው በመለስ ዜናዊ በራሱ ሳይሆን “በአፈ-ንጉሡ” የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር በኩል መምጣቱ ብቻ ነው። ከዚህ በተቀረ ዛቻውም ማባበያውም ለውጥ የለባቸውም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ መሰሪ አካሄድ ጠንቅቆ የሚያውቅ ድርጅት ነው። መለስ ይገላል፣ ያስፈራራል፣ ያስራል፣ ያባብላል። ከዚህ በፊት በዚህ እኩይ ተግባሩ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ምን ያህል እንደተጎዳ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

ዛሬ ሙስሊምና ክርስቲያን፣ ወንድና ሴት፣ ከተሜና ባላገር፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ያሉ ዜጎች በአጠቃላይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ተነስቷል። መለስ ዜናዊና ቡድኑ ይህን ኅብረት ለመበተን የማይፈለቅለው ድንጋይ አይኖርም። እኛ ግን ይህን እድል ልንሰጠው አይገባም።

ግንቦት 7፣ በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ የሚመጣበት ወቅት ላይ ደርሰናል ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ወቅት ለሚመጡ የመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያዎችና ማዘናጊያዎች ጆሮዎቹን መድፈን አለበት ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ - ሙስሉሙም ክርስቲያኑም - በመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያዎችና መሸንገያዎች ሳይበገር ለእኩልነትና ለፍትህ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብሎ ያምናል።

የትግላችንም ስትራቴጂያዊ ግብ መለስ ዜናዊና ቡድኑን ከሥልጣን ማስወገድና በምትኩ የሃይማኖቶችና የሰው ልጆች እኩልነት የተረጋገጡባት፤ ፍትህ የነገሠባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት እንደሆነ ግንቦት 7 በድጋሚ ያረጋግጣል ። ለዚህ የተቀደሰ ተግባር “ሁላችንም በጋራ እንነሳ፤ ለመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያና ማባበቢያ አንበገር” ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!**

## በመለስ ዜናዊ የሚመራው አገዛዝ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል በመፈጸምና የህዝቡን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የጥናቱ አቅራቢ የአምነስቲ ኢንተርናሺናልን ሪፖርት በዋቢነት ጠቅሰው እንዳሳዩት እ.ኤ.አ ከመጋቢት እስከ ህዳር 2011 ብቻ 108 የተቃዋሚ ድርጅት አባላት በቁጥጥር ስር ውለው በዓለም አቀፍ ደረጃ በተወገዘው ጸረ-ሽብር ህግ የሃሰት ክስ ተመስርቶባቸዋል።ከነዚህ ሌላ በውጪ የሚኖሩ ስድስት ጋዜጠኞች፣ ሁለት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና አንድ የሰብአዊ መብት ተሟጋችም እንዲሁ በዚሁ ህግ ተከሰዋል።

በቅርቡ የጋዜጠኝነት ሙያቸውን በማከናወናቸው ብቻ እያንዳንዳቸው አስራ አራት ዓመት እስራትየተፈረደባቸው ሁለት ጋዜጠኞችና በሌለበት እድሜ ይፍታህ የተወሰነበት ኤሊያስ ክፍሌ ህግ የማይገዛው የመለስ መንግስት "ፍትህን" አይበጁኝም ያላቸውን ንጹሀን ዜጎች ለመወንጀያና ለመምቻ እያዋለው ለመሆኑ ማሳያ ነው።አሁንም ታዋቂውን የብዕር ሰው እስክንድር ነጋን ጨምሮ ሃያ አራት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች በፍትህ ስም እስከ ሞት የሚያደርስ የሃሰት ክስ ተመስርቶባቸው በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ ሲሉ ግራሃም ፒብልስ በዳሰሳ ጥናታቸው አመላክተዋል።

ብዙዎቹ የዚህ ጥቃት ሰለባዎች መጀመሪያ የሚታሰሩት ማዕከላዊ እየተባለ በሚጠራው የማሰቃያ እስር ቤት ሲሆን በዛም ከፍተኛ ሰቆቃ ከተፈጸመባቸው በኋላ ያልፈጸሙትን ወንጀል ፈጽሜአለሁ በማለት እንዲፈርሙ ይገደዳሉ።ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ተገደው ማመናቸውን ቢገልጹም ከተላላኪነት ያልዘለለ ሚና የሚጫወተው ይኸው ተቋም ለማጣራት አንዳችም ሙከራ ሳያደርግ የታዘዘውን ብቻ ይወስናል ነው ያለው ጥናቱ።

እናም የኢትዮጵያ መንግስት የሚታመን አለመሆኑን ከግምት በማስገባት ያቺን ሀገር የሚረዱ ዓለምአቀፍ አካላት በራሳቸው ገለልተኛ ገምጋሚ ቡድን በማሰማራት የፍትህ ስርዓቷን ሊፈትሹ ይገባል።የተባበሩት መንግስታትም በቻርተሩ መሰረት ለሰው ልጆች ነጻነት፣የራስን እድል በራስ ለመወሰን መብትና ለፍትህ በመቆም ሀላፊነቱን ሊወጣ ይገባል በማለት ጥናቱ አብራርቷል።

በማያያዝም ለዚህ ግፈኛ ስርዓት በገፍ የሚረዱት እነዚሁ አካላት የስርዓቱ አቀንቃኞች የግል ንብረት እንዳይንቀሳቀስ በማገድ፣ በተመረጡ ኢላማዎች ላይ ማእቀብ በመጣልና ሌሎችም የፖለቲካ ጫናዎችን በማድረግ በስርዓቱ የሚፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ህዝብ የማሰቃየት ተግባራት እንዲገቱ የማድረግ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ አሳስቧል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታዩት ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣የመደራጀትና የሚዲያ ነጻነት ፍጹም አምባገነን አፈናዎች ዋናው ተጠያቂ መለስ ዜናዊ ነው በማለት የሚተነትነው የዳሰሳ ጥናቱ ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ በሃይል፣በማስፈራራትና በእስር የሰፈነው እመቃ ያበቃ ዘንድ እኛ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ አባላት የሚጠበቅብንን ማድረግ አለብን ሲል አክሏል።

በመሆኑም ዓለምአቀፍ ህግንም ሆነ የራሱን ህገ መንግስት የሚጥሰው የኢትዮጵያ ጸረ-ሽብር ህግ በአስቸኳይ እንዳይሰራ ተደርጎ በእስር ቤት የሚገኙት ንጹሀን ሰዎች እንዲለቀቁ ግፊት ሊደረግ ይገባል ነው ያለው ጥናቱ።

ጥናቱ በመጨረሻም ዓለምአቀፉን ማህበረሰብ ሀላፊነቱን እንዲወጣ ስንጠይቅ የጉዳዩ ባለቤቶች እትዮጵያዊያንንም ዝም ብላችሁ አትቀመጡ፣የደፋችሁትን አንገታችሁን ቀና አድርጋችሁ እውነታውን ተጋፈጡት ማለት እንወዳለን በማለት አጠቃሏል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ

**ለኢትዮጵያ አንድነትና ለህዝብ ነጻነት ሁላችንም በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ በጋራ እንነሳ!**

መግለጫ - ሚያዚያ 26: 2004

*ጥምረት ለነጻነት፡ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ* (***ጥምረት***) እንደ ወትሮው ያለፉትን ሶሶት ወራት የሀገራችንን የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርብ ተከታትሎአል። ባለፉት ጥቂት ወራትና ሳምንታት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰው ግፍና መከራ ሌላ እመርታ አሳይቶአል። የወያኔ አገዛዝ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከየአቅጣጫው የሚያነሱት የመብት ጥያቄዎች ከቁጥጥር ውጭ ሆነዉበት ሰሜን አፍሪካ ዉስጥ የተካሄደው አይነት ህዝባዊ ስርአት አንቀጥቅጥ የለውጥ ማእበል እኔንም ከስልጣኔ ይፈነግለኛል በሚል ጭንቀት ወስጥ ለመሆኑ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች በግልጽ ይጠቁማሉ።የዘረኛው ስርዓት ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባዶ ቃላት እየመነዘረ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል እየታዘብንም ነው።

በተለያዩ የመብት ጥያቄዎች ዙሪያ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ህዝቡ ተግባራዊ መነሳሳትና ተቃውሞ እያሳየ ይገኛል። በጋምቤላ፣በአፋርና፣በኦሞ ፈሰስ ፣በጎንደር የዋልድባ ገዳምና ሌሎችም አካባቢዎች ወያኔ በልማት ስም ህዝቡን እትብቱ ከተቀበረበት ምድር ያለምንም መጠለያና መካሻ እያፈናቀለ ይገኛል። በደቡብ አትዮጵያ ነዋሪ የነበሩ የአማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን በወያኔ በራሪ ድብዳቤ የዜግነት መብታቸው ተጥሶ የዚህ ዘረኛና ግፈኛ ስርአት ሌላው ሰለባ ሆነዋል።

በልማት ስም አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ማፈናቀሉ ሳይበቃው፡ ዋልድባን የመሰሳሉ የሃይማኖት ቦታዎችን በመድፈር በአለም ደረጃ እውቅናና አድናቆት የተስጣቸውን የሀገርቱን የሃይማኖትና የታሪክ ቅርሶች በማውደም ለኢትዮጵያና በቀዳሚነት ለሚወሰሩት እምነቶቿ ወያኔ ያለውን ንቀትንና ጥላቻ ዳግም በገሃድ እያሳየ ነው።

መለስ ዜናዊ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ያነሱትን የመብት ጥያቄ ክብደት ስጥቶ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ በማንቋሸሽና በማናናቅ በአለም ከሚታየው አክራሪ ሂደት ጋር በማገናኘት የምእራቡን አለም ቀልብ ለመሳብና ለዲፕሎማሲያዊ ፍጆታ ሊጠቀምብትም ላይ ታች እያለ ነው። ሁኔታውን በሃይማኖት ልዩነት ላይ ይተመሰረተ ቅራኔ ለማድረግ የወያኔ ዘረኛ ስርአት እያሴረ ይገኛል።

ወያኔ በጠመንጃ ኃይል ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ ሲሰራበት የነበረው ህዝብን በዘር የመከፋፈልና የኢትዮጵያን አንድነት የማናጋት ሴራው እየከሰመ ስለመጣበት ህዝቡን በሃይማኖት ቅራኔ ውስጥ በመዝፈቅ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም እየተፍጨረጨረና እየማሰነ ይገኛል። በቅርቡም የዘረኛው

ስርአት መሪ መለስ ዜናዊ ሃይማኖትን በሚመለከት ለአሻንጉሊት ፓርላማዉ ያቀረበው ሀተታ እጅግ አደገኛ መሆኑንም ***ጥምረት*** ያስገነዝባል።

ጽንፈኝነት በእስላሙም ሆነ በክስርስትያኑ መካከል እየታየ ነው በማለትና በእንጭጩ መቅጨት በሚል ዘይቤ በሰላም አብረው በመኖር የሚታወቁትን የክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን ለማጋጨትና በዚህም ሳቢያ የመብት ጥያቄዎችን በሃይል ለመደምሰስ በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከቅርብ ቀናት በፊት በአርሲ በእስልምና ተከታይ ኦሮሞ ወግኖቻችን ላይ የወሰደው የጭፍጨፋ እርምጃ ይህን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በሁለቱም ዋና ዋና ሃይማኖች ላይ በጠላትነት የተነሳ መሆኑን የቅርብ ሳምንታት ተግባሩ ጉልህ ማስረጃ ስለሆነ የሁለቱም ሃይማኖቶች ተከታዮች ይህን እኩይ ሴራ ተገንዝበው የወያኔ ተንኮል መሳሪያ እንዳይሆኑ ***ጥምረት*** በአጽኖት ያሳስባል።

የሁሉም ጠላት የወያኔ ዘረኛ ስርዓት ስለሆነ ይህን ግፈኛና ከፋፋይ ስርአት ከስር መሰረቱ ለመፈንቀል በህብረት መታገል ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅና ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚሻ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ ዜጋ ለሀገር አንድነትና ለህዝብ መብቶች መከበር እንዲሁም ለነጻነትና ለፍትህ ከዳር እስከ ዳር ይነሳ፤ የወያኔን ዘረኛ ስርዓት ለመናድ አምርረን እንታገል፣ጸረ ወያኔ ትግሉን በመላው አትዮጵያ እናፋፍም በማለት ***ጥምረት*** ሀገራዊና ወገናዊ የትግል ጥሪውን ለሁሉም የፖለቲካ ሃይሎችና ለመላው የኢትዮጲያ ህዝብ በአንክሮ ያቀርባል።

**ውድቀት ለዘረኛው የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ!**
**በተባበረ ትግል ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

**ለግንኙነት: pr@timret.org**

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት በኢትዮጵያ የወያኔው አገዛዝ በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በመጨረሻም ህዝባችን ወያኔ በደገሰለት የሃይማኖት መከፋፈል ወጥመድ ውስጥ እንዳይወድቅ ያስጠነቀቀው መግለጫ የሁሉም ጠላት የሆነውን ይህንን የወያኔ ግፈኛና ከፋፋይ ስርአት ከስር መሰረቱ ለመፈንቀል በህብረት መታገል ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅና ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚሻ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ በመሆኑ እያንዳንዱ ኢትዮጳያዊ ዜጋ ለሀገር አንድነትና ለህዝብ መብቶች መከበር እንዲሁም ለነጻነትና ለፍትህ ከዳር እስከ ዳር ይነሳ፤ የወያኔን ዘረኛ ስርዓት ለመናድ አምርረን እንታገል፣ጸረ ወያኔ ትግሉን በመላው አትዮጵያ እናፋፍም በማለት ሀገራዊና ወገናዊ የትግል ጥሪውን ለሁሉም የፖለቲካ ሃይሎችና ለመላው የኢትዮጲያ ህዝብ አቅርቦአል።

## በሃይማኖት ሽፋን በግልጽና በህቡእ የሃገሪቱን ሰላም ለማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ አካላት ባለቸው የእስልምና . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ ከዜረኛው መለስ ዜናዊ ጽ/ቤት በቀጥታ ተሰጠ በተባለ ትዕዛዝ የሙስሊሙ ህብርተሰብ አይወክለንም በማለት ቅሬታውን ሲያቀርቡበት የነበረው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ምክርቤት መጅሊስ መፍረሱን የመለስ ዜናዊ አማካሪና የፌደራል ጉዳዮች ሃላፊ ሽፈራው ተክለማሪያም የመጇሊሱን አመራር ቢሮዋቸው ጠርተው እንደነገሩት ለማወቅ ተችሎአል። በዚህ ባልተጠበቀ ውሳኔ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በመከፋፈል ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዕድሜ መርዘም ሌት ተቀን ይሰሩ የነበሩ የመጇሊሱ ሃላፊዎች ተደናግጠዋል ተብሎአል።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ተቃውሞውን እያሰማ ያለውን የሙስሊም ህብረተሰብ ለማስፈራራት ደርግ በማርሽ አጅቦ ያሰማ ከነበረው ማስጠንቀቂያ የሚስተካከል መግለጫ አውጥቶ የነበረው የመለስ ዜናዊ ቡድን ህዝበ ሙስሊሙ ማስፈራሪያውን ከቁብ ባለመቁጠር በማግስቱ አርብ ሚያዚያ 26 በብዙ መቶ ሺዎች በመሆን አንዋር መስኪድ ተገኝቶ ተቃውሞውን ሲገልጽ በመታየቱ የወያኔው ቁንጮ በማስፈራራት ሊቀጥል እንደማይችል አውቆ ሃሳቡን በመቀየር ታማኝ አገልጋዮቹ የነበሩትን የመጇሊሱን አመራሮች ለማባረር እንደ ወሰነ ውስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ።

ከሃላፊነታቸው የተባረሩት የመጇሊሱ አመራሮች በየክልሉና በየወረዳው የሚገኙትን ተጠሪዎቻቸውን ስለውሳኔው እንዲያሳውቁ ትዕዛዝ ተሰጥቶአቸዋል ተብሎአል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተቀሰቀሰው ተቃውሞ የተደናገጠው የመለስ ዜናዊ ቡድን የሙስሊሙን ጥያቄ ለማክሸፍ እንቅስቃሴውን እንደተለመደው ከአክራሪነትና ከሽብርተኝነት ጋር ለማያያዝ ሲጥር የቆየ ቢሆንም ከመሃል አዲስ አበባ አልፎ በየክልሉ የተቀጣጠለውና በመቶሺዎች የሚቆጠር ህዝብ ባለማቋረጥ ለሳምንታት አደባባይ ወጥቶ ድጋፉን በመግለጽ ላይ ያለውን የመብት ጥያቄ በሃሰት ውንጀላና ማስፈራሪያ ሊወጣው እንዳልቻለ አመልካች የሆነው ይህ ውሳኔ የብዙዎች ጥያቄ ያለመለሰ በመሆኑ ተቃውሞው እንደሚቀጥል እየተነገረ ነው።

ከዘመናዊ መገናኛ ዘርፎች አንዱ በሆነው የፌሥ ቡክ እየተሰራጨ የሚገኘው አንድ መረጃ እንደሚያሳየው የፊታችን አርብ ተመሳሳይ ተቃውሞ በአዲስ አበባ መስጂድ እንደሚደረግ ይጠበቃል።

## የአሳሳ ከተማ ህዝብና የሟች ቤተሰቦች አርብ ሚያዚያ 19 ቀን 2004 ዓም በጁማ ጸሎት ላይ በወያኔ ታጣቂዎች ለተገደሉ ንጹሃን ዜጎች ሞት ይቅርታ ያድርግልን ሲል የወረዳው ተጠሪዎች ጠየቁ

ባለፈው ሃሙስ ሚያዚያ 26 ቀን በአሳሳ ከተማ ውስጥ ፖሊስ ከወረዳው የወያኔ ቅጥረኞች ጋር የድምጽ ማጉያ ይዞ ከሰፈር ሰፈር በመንቀሳቀስ ባደረገው ለፈፋ የከተማው ህዝብና የሟች ቤተሰቦች ሚያዚያ 19 ቀን ለጁማ ጸሎት በተሰበሰበው የሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ ፓሊስ በከፈተው የተኩስ እሩምታ ህይወታቸው ላለፈው ንጹሃን ዜግች ይቅርታ መጠየቁንና ለያንዳንዱ ሟች ቤተሰብ በነፍሰወከፍ 15000 አስራ አምስት ሺህ ብር ካሳ እንደሚከፍል ማሳወቁ ብዙዎችን እንዳስቆጣ ከስፍራው የደረሰን ዜና አመለከተ።

ሰውን የሚያክል ፍጡር በጠራራ ጸሃይ በጥይት ደብድቦ ከገደሉ ቦኋላ የአንድ እርድ በሬ መግዣ ዋጋ ካሳ ውሰዱ ብሎ መለፈፍ ለሟቾች ህይወት ብቻ ሳይሆን ለኛ ለቀሪዎቹም ንቀት ነው ያሉት የከተማው ነዋሪዎች ወያኔ ሥልጣን ከያዜ ወዲህ በተለያየ ቦታ ለሚገድላቸው ንጹሃን ዜጎች ሃላፊነት ወስዶና ይቅርታ ጠይቆ እንደማያውቅ እየታወቀ የአሁኑ ይቅርታና የ15 ሺህ ብር ካሳ በከተማው ውስጥ የተነሳውን ህዝባዊ ቁጣ ያበርዳል ከሚል የፖለቲካ ስሌት እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ሆኖአል ብሎአል።

የአሳሳ ከተማ ህዝብ ሆይ፤ ይህ በከተማችን የተፈጸመው ግዲያ የፈጠረው ሃዘን ከኛ አልፎ የኦሮሚያን ክልል መንግሥት እጅግ አሳዝኖታል። የሞተን ነፍስ መመለስ እንደማይቻል ታውቆ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ለሟቾች ቤተሰብ መጽናኛ ለያንዳንዱ ሟች 15 000 አስራ አምስት ሺህ ብር ካሳ ይከፍላል። እንደምታውቁት ነፍስ መልሰን መዝራት አንችልም። ይልቁንም የሟቾች ቤተሰቦች ከአሁን ቦኋላ የሚገጥማቸውን ችግር የወረዳውና የዞኑ አስተዳደር እየተከታተለ ይረዳቸዋል። ሁላችሁም ከልብ አድምጡ። ከሟቾች አንዱ የ9 ቤተሰብ አስተዳዳሪ እንደሆነና በርሱ አለመኖር የቤተሰቡን ጉዳት መጠን መገመት አያዳግትም። ፤ ሌላኛው የሁለት ልጆች አባትም እንዲሁ። ገና የ12 አመት ታዳጊ የነበረው ወጣት ባይሞት ኖሮ ለኦሮሚያ ሊያበረክት ይችል የነበረው ምን እንደሆነ አይታወቅም። ይህ ሁሉ ሃዘናችንን ጉልህ አድርጎታል። ስለዚህ የሟቾች ቤተሰቦች ብቻ ሳትሆኑ እናንተም የከተማው ነዋሪዎች ሁላችሁም ይቅር በሉን ። እንዲህ አይነት የከፋ አደጋ መልሶ አያግኛችሁ። አምላክ ከ እንዲህ አይነት አደጋ ይሰውራችሁ; ይቅር በሉን። ከልባችን ሆነን ይቅርታችሁን እንማጸናለን። በማለት ነዋሪዎችን ለማዘናጋት ተሞክሮአል። የአሳሳ ህዝብ ከተገደሉት ልጆቹ በተጨማሪ በዚያን ዕለት ታፈሰው ከታሰሩ በርካታ የአገር ሽማግሌዎች፤ ሴቶችና ወጣቶች አሁንም ገና በ እስር ላይ የሚገኙ እንዳሉ በሃዘን ይናገራል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው አርብ በታላቁ የአንዋር መስጊድ ለፀሎት በተሰበሰቡ ምዕመናን መካከል ሁለት የመካከለኛው ምሥራቅ ዜጎች በመግባት ህገ-ወጥ ቅስቀሳ ሲያደርጉ እና በህገ -ወጥ መንገድ ወረቀት ሲበትኑ ተገኝተው ከአገር ተባረዋል በማለት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ባለፈው እሁድ ያስራጨው ዜና የተለመደው የወያኔ ፈጠራ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ማጣጣላቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ተሌቪዝን ኢሳት በትናንትናው ዜናው መዘገቡ ታወቀ።

በጉዳዩ ዙሪያ የ ኢሳት ዘጋቢዎች ያነጋገሯቸው በርካታ የመዲናይቱ ነዋሪዎች:-” ከመሬት ተነስቶ ንፁህን ዜጎችን በሽብርተኝነት የሚከስ መንግስት፤ አንዋር መስጊድ ውስጥ ገብተው ህገ-ወጥ ቅስቀሳ ሲያደርጉና ወረቀት ሲበትኑ የያዛቸውን የውጪ አገር ዜጎች እንዲሁ ዝም ብሎ ከአገር ያስወጣል ማለት የማይመስል ነጭ ውሸት ነው” ማለታቸውን ገልጾአል።

ከአገር እንዲወጡ ተደርገዋል የተባሉት ሁለት የውጪ አገር ሰዎች በደፈናው :-”የመካከለኛው ምሥራቅ ዜጎች” መባላቸው እና በትክክል የየትኛው አገር ዜጎች እንደሆኑ አለመገለጹም፤ ሌላው የዜናውን ተዓማኒ መሆን እንድንጠይቅ የሚያደርገን ነጥብ ነው ብለዋል-ነዋሪዎቹ ያለው ኢሳት በጋዜጠኝነት ሙያ የምርመራ ሪፖርት ለማጠናቀር ወደ ኢትዮጵያ ሊገቢ ሲሉ የተያዙትን የስዊድን ጋዜጠኞች፤ “ያለ መግቢያ ወረቀት ከኦጋዴ ነፃነት ግንባር ታጣቂዎች ጋር ወደ አገር ሊገቡ ሞክረዋል” በማለት በሽብርተኝነት የከሰሰ መንግስት፤ በሙስሊሞች ተቃውሞ በተወጠረበት በአሁኑ ጊዜ:-”ተቃውሞው መሀል አመጽ የሚቀሰቅሱ የውጪ ዜጎችን ይዤ እንዲሁ ወደ አገራቸው አባረርኳቸው” ብሎ በዜና ማሳወጁ፤ባለሥልጣናቱ ምን ያህል የተራ ዱርዬ ተግባር ውስጥ መግባታቸውን ያሳይ ካልሆነ በስተቀር፤ ማንንም የሚያሳምን አይደለም”ሲሉም አክለዋል ብሎአል።

ሀይማኖታዊ መብታቸውን ለማስከበር ህጋዊ እና ሰላማዊ ጥያቄ እያነሱ ያሉትን ብዙሀን ሙስሊሞች፤ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንዲሉ በውጪ ሀይሎች ድጋፍ እንደሚደረግላቸው መንግስት በተደጋጋሚ ክስ ሲያሰማ መቆየቱን ያስታወሱት የመዲናይቱ ነዋሪዎች፤ እንደተባለው ሁለቱ የውጪ ዜጎች አመጽ ሲቀሰቅሱ ቢያዙ ኖሮ ለመንግስት ክስ ጥሩ ማስረጃ በሆኑት ነበር”ብለዋል።

## በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ባስነሱት ተቃውሞ በርካቶች መታሰራቸው ተዘገበ

ተቃውሞው ምግብን ሰበብ አድርጎ እንደተፈጠረ ቢነገርም፣ የተማሪዎች ግን ከዚህ የዘለለ ነው ተብሎአል። ትናንት ከሰአት በሁዋላ የተነሳው ተቃውሞ ዛሬም ቀጥሎ የዋለ ሲሆን ተቃውሞው ከዞኑ ፖሊስ አቅም በላይ በመሆኑ የፌደራል ፖሊስ ጣልቃ ገብቷል። ተማሪዎች በፖሊሶች ላይ የሚያወርዱት ድንጋይ መምህራኑ ከግቢያቸው እንዳይወጡ አድርጓቸው እንደነበር የደረሰን መረጃ ያመለክታል። የፌደራል ፖሊስ ግቢውን ለመቆጣጠር መሳሪያዎችን መተኮሱን አድማ በታኝ ጭስ መጠቀሙን ለማወቅ ተችሎአል። እስካሁን በግጭቱ ምን ያክል ሰዎች እንደሞቱ ለማወቅ ባይቻልም በርካታ ተማሪዎች ተይዘው መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። በተቃውሞውም በዩኒቨርስቲው ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ይህን ዜና እስካጠናቀርንበት ጊዜ ድረስ ተቃውሞው እንደቀጠለ ነው።

### ወያኔ ተጨማሪ ፖሊስና መካለከያ ሰራዊት ውጥረት ወደነገሰበት ጋምቤላ ለማዝመት እንቅስቃሴ ላይ . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

“እየጨረሱን ነው፤ ብቀላው ተጀምሯል፤ ድረሱልን” ሲል ለኢትዮጵያን እና ለዓለም አቀፍ መንግስታት ተማጽኖ እያሰማ ነው ብሎአል። “ተማጽኖው በሥሙ ወንጀል እየተፈጸመ ላለው የትግራይ ህዝብም ጭምር መሆኑን የገለጸው ንቅናቄ “ድፍን የአኙዋክ ብሄረሰብ አባላት በሽፍትነት ተፈርጀናል፣ ችግሩ አሳሳቢ ነው። በቀሉ ተጀምሯል። አሁን እየተካሄደ ያለው ግድያ በ1996 ከተካሄደው ጭፍጨፋ የሚተናነስ አይደለም። አገርና ህዝብ ከጠላት ለመጠበቅ የማለ ሠራዊት፤ የራሱን ህዝብ እንዲጨርስ ታዟል። እንዲህ ያለ ተግባር የጠላት ሠራዊት እንኳን አያከናውንም” በማለት የአካባቢው ህዝብ እያማረረ መሆኑን ዘግቦአል።

ለጋራ ንቅናቄው መረጃ የአይን እማኝነት ምስክራቸውን የሰጡ አንድ ግልሰብ በቅርቡ አንድ የአካባቢው የአገር ሽማግሌ፤ በአገራቸው ባህል መሰረት ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ሳለ፣ የህወሃት/ ኢህአዴግ የመከላከያ አባላት ድንገት ወደተቀመጡበት በመምጣት “ለሽፍቶች ቀለብ የምትሰጠው አንተ ነህ” በማለት ለወሬ ነጋሪነት አንዳቸውንም ሳያስተርፉ አዛውንቱን እስከነ ቤተሰቦቻቸው መረሸናቸውንና “እንዲህ ያለው አሰቃቂ ተግባር የሚፈፀመው መለስ ዜናዊ በሚመራው ህወሃትና በትግራይ ህዝብ ስም ነው” በማለት እያለቀሱ መናገራቸውን ገልጾአል።

ከዚህ በተጨማሪ ተገድለው ጫካ ውስጥ ከተጣሉ ቦኋላ የበሰበሰው የአስከሬናቸው ጠሬን ያሉበትን ስፍራ ያመለከተ ዜጎች እንዳሉ፤ መምህራንና ተማሪዎች እየደረሰ ባለው የጅምላ ጭፍጨፋ ተደናግጠው ከመማር ማስተማር ተግባራቸው እየተስተጓጎሉ እንደሆነ፤ የዕድሜ አዛውንቶችና እናቶች በጥቃቱ ሰለባ በሆኑ ወጣት ልጆቻቸው መገደል ምክንያት ጧሪ ዘመድ አልባ እየሆኑ እንደመጣ በሰፊው ዘግቦአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz
ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org